# ቅድስት መስቀል ክብራ

ጌታቸው በቀለ

«የሽማግሌ መካሪ፥ ፊት ተናጋሪ አይንሳህ» እንዲሉ አበው የመስቀል ክብራ ገድል የት እንደሚገኝ አንድ አባት ብጠይቃቸው በአንቀጸ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከገድለ ላሊበላ ጋር እንደሚገኝ ነገሩኝ:: ወደ ተጠቆምኩት ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ለደብሩ ጽ/ቤት ከየት እንደ መጣሁ ገልጬ ቀን ቀጠሮ ሰጡኝ:: በተቀጠርኩበት ቀን ተገኝቼ የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ኃይል ኃይለ ኢየሱስ ተመስገን ፈቅደው ክብራናው ላይ ማእዙን እንዲተረጉሙልኝ የቅኔ መምህር የሆኑትን መልአከ ሕይወት ፍሬ ስብሐት ጸጋዬን አዘው ከገድለ ላሊበላ ላይ «የመስቀል ክብራን» ታሪክ እንድጽፍ ስላደረጉልኝ መልካም ትብብር በእግዚአብሔር ስም ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ::

በሀገራችን ኢትዮጵያ በሃይማኖት፣ በምግባረ ሠናይ የጸኑ አያሌ ቅዱሳት እናቶች እንደነበሩ የታወቀ ነው:: በእምነታቸው፣ በመልካም ሥራቸው፣ በተጋድሎአቸው በቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቅዱሳን ከሰፈሩት፣ ከታወቁት አንዷ ቅድስት መስቀል ክብራ ናት:: መስቀል ክብራ በወሎ ሀገረ ስብከት በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነገደ አበው ተወለደች:: ወላጆቿም እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ ሰውን የሚወዱ፣ የሚያከብሩ ደጎች ስለነበሩ ልጃቸውን የሃይማኖት ትምህርት አስተምረው በምግባረ ሠናይ አሳደጓት:: ለዐቅመ ሔዋን በደረሰች ጊዜ በብሥራተ ቅዱስ ገብርኤል መስቀል ክብራና ላሊበላ እንዲገናኙ ፈቃደ እግዚአብሔር ሆነ::

የመስቀል ክብራ ታሪክ ከጻድቁ ንጉሥ ከላሊበላ ጋር ተያያዥነት (አንድነት) አለው:: ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ የተመረጠው ላሊበላ ሲወለድ የንብ ሠራዊት ከቤተ መንግሥት ገብቶ መላ አካላቱን ወሮት ዙሪያውን ሰፍሮበት ነበር:: እናቱም ተደንቃ «ልጄ ማር ይበላል፤ ለልጄ ንብ ዘበኛ ሆኖ ይጠብቀልኛል» ስትል «ላል ይበላ» ብላ ስም አወጣችለት:: በአገው ቋንቋ «ላል» ማለት ንብ ማለት ነው:: «ላል ይበላል» ማለት በቁሙ «ማር ይበላል» ማለት ነው:: መልካም ስም ጥሩ ንጉሥ ይሆናል ስትል «ላል ይበላ» ብላዋለች:: ከጊዜ በኋላ ላሊበላ ተባለ:: በዚያን ወቅት ወንድሙ (ሐርቤ) ስመ መንግሥቱ ገብረ ማርያም ንጉሥ ነበር:: የአባቱ ልጅ እኅቱ በጊዜው ለነገሠው ወንድሟ በማድላቷ ላሊበላን ልትድገለው ባቀደች ጊዜ ከሰው ጋር ከመቀመጥ ከዱር አራዊት ጋር መቀመጥ ይሻላል ብሎ ወደ ሌሷ አውራጃ ተሰዶ በዱር፣ በጫካ ተቀመጠ:: ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘው ቅዱስ ገብርኤል ወደ ላሊበላ መጥቶ፦ ላሊበላ ሆይ፥ ሰላምታ ይገባሃል አለው:: ላሊበላም እንደዚህ ያለ ሰላምታ የምታናግረኝ አንተ ማነህ? አለው:: «ወይቤሎ አነ ውእቱ መልአክ እግዚአብሔር፤ እኔ አጠብቅህ ዘንድ የሰማይ ምሥጢራትን አሳይህ ዘንድ ወደ ሰማይ ያወጣሁህ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ነኝ» አለው:: ላሊበላም ሰላምህ በእኔ ላይ ይደር አለ:: መልአኩም የምነግርህን አዳምጥ አለው:: ላሊበላም «ጌታዬ ፥ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር» አለው::

መልአኩም ነገ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነችው መስቀል ክብራ ወደ አንተ ትመጣለች፤ የምትለብሰውን ልብሷን፣ ትምህርቷን፣ ልቡናዋን ሁሉ አወቅ «ወይቤሎ ይእቲኬ ዘትከውነከ ብእሲተ፤ ይቺም ረዳት ሚስትህ ትሆንሃለች» እንደ አንተ የተመረጠች ናት፣ ልቧም እንደ አንተ ብሩህ ነው:: ሥራዋም ከአንተ ሥራ የማያንስ የእግዚአብሔር ማደሪያ ናት አለው:: «ወብዙሃ ምግባረ ሠናይ ትትሜሃር እምኔሃ፤ አንተም ከሷ ብዙ ምግባረ ሠናይ ትማራለህ» እንደ ነገርኩህ ሁሉን ንገራት:: ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ነው:: እነግርህ ዘንድ ታዝዣለሁና» አለው:: ላሊበላም መልአኩን ጌታዬ ሆይ! ሰባቱ ሰማያትን ካሳየኸኝ በኋላ ሚስት አገባ ዘንድ ይገባኛልን? እያለ ተከራከረው:: ቅዱስ ገብርኤልም «ኃጢአትኑ ነሢአ ብእሲት፤ የእግዚአብሔር ሰው ላሊበላ ሆይ! ሚስት ማግባት ኃጢአት ነውን? ሚስት በማግባት ክብርህ አይጐድልም:: ዓለምን በመውደድ ሳይሆን ዘር ለመተካት ስለሆነ ነው:: የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ልትዳፈር ይቻላልን? ወይስ ዘርን ብቻህን ማስገኘት ትችላለህን?» አለው:: ከዚህ በኋላ ላሊበላ የእኔ ፈቃድ ቀርቶ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን አለ:: ያን ጊዜ መልአኩ ከርሱ ተሰወረ::

ይህን በተነጋገሩ በማግሥቱ ከዱር ቅጠሎችን እየለቃቀመች መስቀል ክብራ መጣች:: መልአኩ እንደ ነገረው ምልክቱ ሁሉ ትክክል ሆኖ አገኘው:: መልአኩ የነገረውን ነገራት:: መስቀል ክብራም ነገሩ ደስ አላት:: የሚነግራት ሁሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ነውና:: ከዚህ በኋላ ከእናት አባቷ ቤት የሚበላውን፣ የሚጠጣውን እያመጣችለት እየተመገበ በተገናኙበት ቦታ ብዙ ጊዜ ተቀመጠ:: ላሊበላ መስቀል ክብራን የምነግርሽን ሁሉ ለአባትሽ ንገሪ አላት:: መልአኩ የነገረውን ሁሉ ነገራት:: መስቀል ክብራም የነገራትን ወደ ቤቷ ሄዳ ለአባቷ ነገረችው:: «ወአቡሃሰ ፈራሄ እግዚአብሔር ውእቱ፤ አባቷ እግዚአብሔርን የሚፈራ ደግ ነበርና» አባቷ ይሄ ከመሆኑ በፊት የሚሆነውን ሁሉ ያውቅ ነበር:: መስቀል ክብራን «ሂደሽ ልጁን ጥሪው» አላት:: እሷም ሄዳ ላሊበላን ይዛው መጣች:: አባቷ ካለበት በደረሰ ጊዜ እጅ ነስቶ ሰላምታ ተሰጣጡ::

የመስቀል ክብራ አባት ላሊበላን «ልጄ ሆይ! ልጄን ለምን ፈለግሃት? አለው ላሊበላም በራሴ ፈቃድ ተነሣስቼ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ስለሆነ ሳይፈጸም አይቀርም:: ከሰው የሆነ ነገር ሁሉ ያልፋል፤ ይሻራልና» አለው::

በኋላም አባትየው መስቀል ክብራን የጠራላት፣ ያገናኘው፣ ያሳየው መልአከ እግዚአብሔር እንደሆነ አወቀ:: የመስቀል ክብራ አባት ሚስቱን ጠርቶ ልጃቸውን ለላሊበላ ይሰጡ ዘንድ ከሚስቱ ጋር ተመካከረ «ወሠምረት ብእሲቱ በዝንቱ ነገር፤ ሚስቱም በዚህ ነገር ደስ አላት» ላሊበላ በሰማይ እንደሚያበራ ፀሐይ በእግዚአብሔር ጸጋ ግርማው ያማረ ነውና፣ አባት እናቷም እንደ እግዚአብሔር ሕግ ሚስት ትሆነው ዘንድ መስቀል ክብራን ለላሊበላ ሰጡት:: በፈቃደ እግዚአብሔር የተገናኙ ናቸውና የፈጣሪውን ትዕዛዝ አክብሮ ከእናት አባቷ ጋር ተነጋግሮ በሕግ፣ በሥነ ሥርዓት አገባት:: ይስሐቅ ርብቃ እንደተባረከ፣ ላሊበላም ፈቃደ እግዚአብሔርን እየፈጸመ ወንጌል እየሰበከ መስቀል ክብራን ካገኘ እንስቶ ምስጋናውን አበዛ::

መስቀል ክብራ እግዚአብሔርን የምትፈራ ናት:: ለአብርሃም ሣራ እንደምትታዘዝና ጌታዬ እንደምትለው በሷ ምክርም ይሄድ እንደነበር ሁሉ ላሊበላም በመስቀል ክብራ ምክር ይሄዳልና፣ ወደ ግራም ወደ ቀኝም ሳይል ከሚስቱ ምክር አይወጣም ነበር:: የመስቀል ክብራ ቃሏ ለእሱ ከማር ከስኳር ይበልጥ ይጣፍጠዋል:: የላሊበላ ቃሉም ለእሷ ከወይን ወለላ ይበልጥ ይጣፍጣታል:: ሃይማኖታቸውን ጠብቀው በእግዚአብሔር ፍቅር ጸንተው ኖሩ:: አንድነታቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና:: ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ፦ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ... ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው



www.ethiopianorthodox.org

እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው» እንዳለ ማቴ.19፥4–6። የመስቀል ክብራና የላሊበላ አንድነት በዚህ ዓለም በሚሰራው በአጋንንት ዘፈን ሳይሆን በእግዚአብሔር ሕግ የጸና ነው። እንደ ይስሐቅና ርብቃ ጋብቻ ነበር። ይህም በመሆኑ በፍቅር፣ በትኅትና እግዚአብሔርን እያገለገሉ ብዙ ዘመን ኖሩ።

የሰው ጠላት የሆነው ዲያብሎስ የመስቀል ክብራንና የላሊበላን ግብራቸውን፣ አንድነታቸውን፣ ፍቅራቸውን፣ ሕይወታቸውን ባየ ጊዜ ቀና። በሰዎች ኅሊና ገብቶ ተነሣቸው። በተለይ የንጉሡ ወዳጅ ነን የሚሉ ክፉዎች ሰዎች በመስቀል ክብራና በላሊበላ ላይ አነሣሳቸው ወደ ንጉሡ ሄደው ከንጉሡ ጋር ያጣሉት ዘንድ፤ አይሁድ በጌታችን ላይ እንደተነሣሡ ሊቀ ካህናትም አሳልፈው እንደሰጡት ሁሉ በላሊበላ ላይም ዲያብሎስ ያነሣሳቸው ሰዎች ለንጉሥ ሐርቤ ከሰሱት፦ «ላሊበላ የሚባል ሰው ለአንድ ምስኪን የታጨች ልጅ ቀምቶ ሚስት አደረጋት፣ ንጉሥ ሆይ፥ ዝም አትበል አንድ ርምጃ እንዲወሰድበት ያስፈልጋል። በሱ ላይ አንድ ነገር ካላደረግህ መንግሥትህ አይታወቅም፤ ዝም ብትል ግን ባለሥልጣኑ እኔ ነኝ በሕዝቡም ላይ እነግሣለሁ ይላል» አሉት፤ ይህን በሰማ ጊዜ ተቆጥቶ ያመጡት ዘንድ አዘዘ።

እነዚያ ከንጉሡ የተላኩ ሰዎችም፦ ላሊበላን አግኝተው «ንጉሥ ይፈልግሃል አሉት።» ላሊበላም፦ «ስለምን ይፈልገኛል፤ ከሱ ተሰድጄ፣ ከሠራዊቱም ርቄ ከምኖርበት ለበጐ ነገር አይደለም የጠራኝ፤ ሊጣላኝ ፈልጐ እንጂ፤ በዳዊት ላይ የሳኦል ልብ እንደተነሣሣ፣ በመንግሥቱ ቅናት የተነሳ ይገድለው ዘንድ እንደፈለገ፣ ንጉሡም በኔ ላይ እንደዚያ ነው። ከዚህ መኖሬን ማን ነገረው፣ ከዱር ወደ ዱር፣ ከበረሃ ወደ በረሃ አይደለም ያለሁትን? ዳዊትና ሳኦል ወንድማማች አልነበሩም? ዳዊት ከሳኦል ፊት እንደሸሸ፤ እኔም በወንድሜ ምክንያት ተሰድጄ፣ ከወንድሜም ርቄ በተወለድኩበት ተጠልቼ ኖርኩኝ፣ አሁንም ወንድሞቼ ሆይ! የተጠራሁበትን ምክንያት ንገሩኝ» አላቸው።

«የተጠራህበትን የምታውቀው እዛው ስትሄድ ነው» ብለው ወስደው ከንጉሡ ፊት አቀረቡት፦ ንጉሥ ሐርቤም «አንተ እንዴት ብትደፍር ነው– በዘመኑ መንግሥቴ የሌላ ሰው እጮኛ ቀምተህ ያገባኸው? በእኔ መንግሥት የማይገባውን ሥራ ለምን ሠራህ? ለሰው የታጨችውንስ እንዴት ወሰድክ?» አለው። ላሊበላም ንጉሡን «ይፈቀድልኝ ልናገር አለ?» ንጉሡም እንዲናገር ፈቀደለት። ላሊበላም «እግዚአብሔር ያላዘዘኝን፣ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የሠራሁት የለም፤ የቀማሁትም የለም፣ መጥፎ ሥራ አልሠራሁም። በሕግ በሥነ ሥርዓት በእናት አባቷ መራቂነት ነው ያገባኋት» አለ። እነዚያ የተላኩ የንጉሡ ሠራዊቶችም የሐሰት ምስክር ሆነው ቀረቡ፣ «ለሌላ የታጨችን ሴት ሲወስድ እናውቃለን» አሉ። ንጉሡም የሐሰት ምስክር አስመስክሮ በጅራፍ ይገርፉት ዘንድ አዝዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስቀደስ ሄደ። ገራፊዎቹም ቁጥሩን ተሳሳትን እያሉ ከሦስት ሰዓት በላይ እየተፈራረቁ ሲገርፉት ዋሉ።

ላሊበላም «አቤቱ ጌታዬ፥ መገረፍ ቀርቶ መወቀስ የማይገባኝ ስሆን እንደ ቸርነትህ አድነኝ፣ ጩኸቴን ስማኝ፣ ፊትህም ተራዳኝ፣ ኃይሌም ሞገሴም አንተ ነህና ከዚህ ወጥመድ አድነኝ» እያለ ይጸልይ ጀመር፤ የተበደሉትን የማይጥል እግዚአብሔር በክንፈ ረድኤቱ ይሰውረው ዘንድ መልአኩን ልኮለት፣ ወርዶ በአክናፈ ረድኤት ጋረደው። ንጉሡም አስቀድሶ ከቤተ ክርስቲያን ሲወጣ የግርፋቱን ድምፅ ሰማና ከሱ ጋር ላሉትም ሕዝቦች «ይህ የምሰማው ድምፅ ምንድን ነው?» አላቸው። «ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትሄድ ላሊበላን ይገርፉት ዘንድ አንተ አላዘዝክምን? እስከ አሁን እየገረፉት ነው። የምትሰማው ድምፅ የግርፋቱ ነው» አሉት። በዚህን ጊዜ ንጉሡ ደነገጠ፤ የሞተም መሰለው፤ ደንግጦ ቀርቦ ቢመለከተው እንኳን የሞት ደረጃ በአካላቱ አባጭ፣ ሰንበር ሳይታይበት በመቅረቱ አድንቆ በነፃ እንዲለቁት አዘዘ።

ላሊበላም ግርፋቱ አልተሰማውም። እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ሚስቱ መስቀል ክብራ ዘንድ ሄዶ የደረሰበትን ሁሉ ነገራት። መስቀል ክብራም በእሷ ምክንያት የባለቤቷ ላሊበላ የደረሰበትን ስቃይ ሰምታ አዘነች። ነገር ግን ይህ ሁሉ ስቃይ ቢፈጸምበትም እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ከዚህ ሁሉ አሰቃቂ ስቃይ በክንፉ ብርሃን ጋርዶ ባለቤቷን ስለአዳነላት እግዚአብሔርን አመሰገነች። ባሏ ከመቅሰፍት ሁሉ ድኖላታልና።

መስቀል ክብራና ላሊበላ ከዚያ ወደ ሌላ አውራጃ ሄደው ተቀመጡ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዞ ወደ አክሱም መርቶ አደረሳቸው። በኋላ ላሊበላን እንዲህ አለው፦ «ገዳማት ግብፅንና በኢየሩሳሌም የሚገኙትን ቅዱሳት መካናት ሳስጐበኝህ ስለታዘዝኩ መስቀል ክብራ በዚህ ትቆይሃለች አጽናንተህ ተሰናበታት» ብሎ ተሰወረ። ንዑድ፣ ክቡር ላሊበላም መስቀል ክብራን ወደ ኢየሩሳሌም ሄጄ ለእኔና ለአንቺ ጸሎት አድርጌ እመለሰለሁና በዚህ ቆይኝ ብሎ ተሰናብቷት ሄደ በምድረ ግብፁ የሚገኙትን ገዳመ አስቄጥስ፣ ደብረ ምጥማቅ፣ ደብረ ቁስቋም፣ ሌሎችንም ገዳማት ተሳልሞ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቅዱሳት መካናትን አይቶ፣ ተሳልሞ ተመለሰ። ኅዳር 6 ቀን በሮሃ ቤተ መንግሥት ነግሠ፣ ንጉሥ ተባለ፤ መስቀል ክብራም ንግሥት ተብላ በንጉሡ ቀኝ ተቀመጠች።

መስቀል ክብራ ላሊበላን አግብታ እርሱ ንጉሥ እርሷ እቴጌ ሆኑ። ቅዱስ ላሊበላ በፈቃደ እግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናትን ሲያሠራ ቅድስት መስቀል ክብራም ከአሥራ አንዱ አብያተ ክርስቲያናት አንዱ የሆነውን የአባ ሊባኖስን ቤተ ክርስቲያን አሠርታለች። ቅድስት መስቀል ክብራ በመስቀል ጦርነት ምክንያት እስላሞች ከባሕር ማዶ እየፈለሱ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ በደስታ እየተቀበለች በእንግድነት ከማስተናገዷም በላይ በግድ ሳይሆን በትምህርት ወደ ክርስትና ሃይማኖት እንዲገቡና እንዲጠመቁ አድርጋለች።

ቅድስት መስቀል ክብራና ቅዱስ ላሊበላ በመልአከ እግዚአብሔር በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት እንዲገናኙና ዘር እንዲተኩ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ በመሆኑ ይትባረክ የሚባል ቅዱስ ልጅ ነበራቸው። ይትባረክ በላስታ የመጨረሻው ንጉሥ ነው።

በኋላም ቅድስት መስቀል ክብራ ዓለምን ንቃ መንና ሄደች። በጾም በጸሎት ተጠምዳ በቀን እልፍ በሌሊት እልፍ እየሰገደች እግዚአብሔርን የምታመሰግን ደግ እናት ሆነች።

በመጨረሻም የቅድስት መስቀል ክብራን እምነት፣ ትሩፋትና ገድል በመመልከት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የቅድስና ክብር ተሰጥቷታል። ለጻድቋ መታሰቢያ የሚሆን እጅግ የሚያስደንቅ በስውር የታነፀ በትግራይ ሀገረ ስብከት በሽሬ አውራጃ መደባይ ታብር በተባለው ቦታ በስሟ ቤተ ክርስቲያን ታንፆላታል። ታቦት ተቀርጾላታል። የዕረፍቷ በዓልም የሚከበረው ሐምሌ 27 ቀን ነው።

የቅድስት መስቀል ክብራና የቅዱስ ላሊበላ ጸሎታቸው፣ ልመናቸው ረድኤታቸው አይለየን። አሜን።


ምንጭ፦
- «ገድለ ቅዱስ ላሊበላ»
- የኢትዮጵያ ታወላጆች ቅዱሳን ታሪክ
- የሴቶች ወንጌላዊ ሕይወት